የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 51
ADDIS ABABA 15th June, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፮/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ከታላቋ ሶሻሊስትና ሕዝባዊ ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ
አዋጅ..... ገጽ ፪ሺ፮፻፶፬

## CONTENTS

Proclamation No. 406/2004

Investments Encouragement and Reciprocal Protection Agreement with the Great Socialist People's Libyan Arab Jamahiriya Ratification Proclamation ...... Page 2654

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፮/፲፱፻፺፮

### ከታላቋ ሶሻሊስትና ሕዝባዊ ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በታላቋ ሶሻሊስትና ሕዝባዊ ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 406/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT SIGNED ON THE ENCOURAGEMENT AND RECIPROCAL PROTECTION OF INVESTMENTS WITH THE GREAT SOCIALIST PEOPLE'S LIBYAN ARAB JAMAHIRIYA

**WHEREAS**, the Agreement on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya is signed in Addis Ababa 27 January 2004;

**WHEREAS**, it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS**, the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Treaty at its session held on 15th day of June,2004

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከታላቋ ሶሻሊስትና ሕዝባዊ ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፮/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና ከታላቋ ሶሻሊስትና ሕዝባዊ ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመነት ኮሚሽን ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመነት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Investment Encouragement and Reciprocal Protection Agreement with the Great Socialist People's Libyan Arab Jamahiriya Ratification Proclamation No. 406/2004."

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement on the Encouragement and Reciprocal Protection of Investment signed in Addis Ababa on 27 January 2004 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya is Ratified.

## 3. Responsibility of the Ethiopian Investment Commission

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement this agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of 15th day of June, 2004

**Done at Addis Ababa, the 15th day of June, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**